ኅዳር ፬ ፳፻፲ ዓ.ም

# ለነጻነት የትግል ጥሪ የተሰጠ ምላሽ

ጸረ ኢትዮጵያዊ የሆነውን ወያኔን ከመሰረቱ ለመለወጥ በውጭ ያለው ሀገር ወዳድ ሀይል በግልም ሆነ በስብስብ የከፈለው አስተዋጽዎ የሚናቅ አይደለም፡፡ ኢትዮጵያን እንደ ሀገር በነጻነት ለማስቀጠል የኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጅቶች በጋራም በተናጠልም ያደረጉትንና እያደረጉ ያለውን ጥረትም ማውሳት ተገቢ ነው፡፡

ይህንን የሀገር ጠንቅ የሆነ የወያኔ ስርዓትን ለማስወገድ የሚደረገውን እልህ አስጨራሽ ትግል ለመደገፍ በውጭ ያለነው ኢትዮጵያኖች በጋራ ግብረ ሀይል ስም ላለፉት አመታት በየቦታው እንቅስቃሴ እያደረግን እንገኛለን፡፡

ዛሬ ሀገራችን ኢትዮጵያና ሕዝቧን ከዚህ የግፍ ስርዐተ ምጥ ለመገላገል የመጨረሻው ደውል እያስተጋባ ይገኛል፡፡ በተለይ የሰሞኑ የወርሀ ህዳር ሕዝባዊ እንቢተኝነት በሀገር ቤት ባሉ ድርጅቶች በጋራ ከተጠራ ወዲህ ለጋራ ጥሪው የጋራ መልስ ለመመለስ ከሰሜን አሜሪካ በርካታ ግዛቶች ፣ ከአውሮፓ ልዩ ልዩ ከተሞች ፣ በአፍሪካ እና በአውስትራሊያ የሚገኙ ተንቀሳቃሽ ሀይሎች ባሳለፍነው የሳምንቱ መጨረሻ ጥልቅ እና ግልጽ የሆነ ሰፊ ውይይት በማካሄድ ህዝባዊ እንቢተኝነቱን ሁለንተናዊ ድጋፍ ለመሆን መግባባትን ፈጥረናል፡፡

በዚሁ በወርሀ ህዳር የተነደፈውን የሀገር ቤት ጥሪ በመርሀ ግብሩ መሰረት እኛም የዜግነት ድርሻችንን ለመወጣት እና ፈጣን ምላሽ ለመስጠት እንዲሁም የህብረትን መደላደል ለመፍጠር ወስነን ሥራ ጀምረናል፡፡ በዚሁ አጋጣሚ በሀገር ቤትም ሆነ በውጭ ያለን ኢትዮጵያዊያን ለሕዝባዊ እምቢተኝነቱ ጥሪ አፋጣኝ ምላሽ በመስጠት ነጻነታችንን እና ክብራችንን እናስመልስ ዘንድ ለጥሪው ጥሪ እናስተጋባለን፤ እንዲሁም በውጭ የሚገኘው ህጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ለሀገር ቤቱ መርሀ ግብር አጠናካሪ የሆነ የጸሎት እና የምህላ ውሳኔውን ስናደንቅ፤ በተጨማሪም ይሄንኑ ሀገራዊ ጥሪ ተቀብሎ ለተግባራዊነቱ ሙሉ አጋርነቱን በመግለጫው ለገለጸው በዋሽንግተን ዲሲ የሚገኘው የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ማእከል የሆነውን የፈርስት ሂጅራ ፋውንዴሽንን ሳናደንቅ አናልፍም። በመጨረሻም በዓለም ዙሪያ ያለነው የኢትዮጵያዊያን የጋራ ግብረ ሀይል የሀገር ቤቱን እንቅስቃሴ እየተከታተልን በመመካከር ተከታታይ የሆኑ ተግባሮችን በመግለጫ እናሳውቃለን፡፡

የአለም አቀፍ የጋራ ግብረ ሀይል ግዚያዊ ኮሚቴን ለማግኘት dcjointtaskforce@gmail.com ወይም 571 403 2474 ይጠቀሙ።

ያለነጻነት ፍትሀዊ ምርጫ አይታሰብም!

ሕዝባዊ እንቢተኝነት ይጠንክር!

ዓለም አቀፍ የጋራ ግብረ ሀይል ግዚያዊ ኮሚቴ